አንድም ነቢይ ለህዝቦቹ ያልተናገረውን ስለደጃል አንድ ነገር አልነግራችሁምን? እርሱ እውር ነው፣ እርሱ ጀነትና እሳት በሚመስል ነገር ከራሱ ጋር ይዞ ይመጣል።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ
(የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "አንድም ነቢይ ለህዝቦቹ ያልተናገረውን ስለደጃል አንድ ነገር አልነግራችሁምን? እርሱ እውር ነው፣ እርሱ ጀነትና እሳት በሚመስል ነገር ከራሱ ጋር ይዞ ይመጣል። እርሷ ጀነት ናት የሚላት እሳት
ናት። እኔ ኑሕም ህዝቦቹን እንዳስጠነቀቀው አስጠነቅቃችኋለሁ።"» [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለባልደረቦቻቸው ስለደጃል፣ ስለባህሪያቱና ምልክቶቹ ከርሳቸው በፊት ማንም ነቢይ ያልተናገረውን ነገሯቸው። ከዚህም መካከል:- እርሱ አንድ‐ዓይና ነው። አላህ ከርሱ ጋር ለዓይን በሚታይ መልኩ ጀነትና እሳት የሚመስልን ነገር እንዳደረገለት፤ ነገር ግን ጀነት መስሎ የሚታየው እሳት፣ እሳት መስሎ የሚታየው ጀነት ነው። እርሱን የታዘዘን ለሰው "ጀነት" መስሎ በሚታየው ውስጥ ይከተዋል። ነገር ግን እርሷ የምታቃጥል እሳት ናት። እርሱን ያመፀን ለሰው "እሳት" መስሎ በሚታየው ውስጥ ይከተዋል። ነገር ግን እርሷ ምርጥ ጀነት ናት። ቀጥለውም ልክ ኑሕ ለህዝቦቹ እንዳስጠነቀቀው ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከደጃል ፈተና አስጠነቀቁን።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/3110